# መርካቶ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ የንግድ ፡ መደብሮች ፡ የሕግ ፡ ግዴታዎችን ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደሚጠብቁ ።

በጆን ፡ ሮዝ ፡ እና ፡ ዘማርያም ፡ በርሄ ።*

የ"ነጋዴነት" ፡ አቋም ፡ ኖሯቸው ፡ በንግድ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የተሠማሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ መከተል ፡ የሚገባቸው ፡ የሕግ ፡ ግዴታዎች ፡ አሉ ። በጣም ፡ ከታወቁት ፡ ግዴታ ዎች ፡ አንዱ ፡ ከንግድ ፤ ኢንዱስትሪና ፡ ቱሪዝም ፡ ዘንድ ፡ ሄዶ ፡ መመዝገብና ፡ ስለሚ ደረጉት ፡ ንግዶች ፡ በሙሉ ፡ ሂሣብ ፡ መያዝ ፡ ነው ። በተጨማሪ ፡ ኪሣራ ፡ ያጋጠማቸው ፡ እንደሆነ ፡ የንግድ ፡ ግዴታዎች ፡ በሙሉ ፡ ሊጠበቁ ፡ ካልተቻለ ፡ ኪሣራ ፡ መግባታቸ ውን ፡ ለከፍተኛ ፡ ፍ/ቤት ፡ ማስታወቅ ፡ አለባቸው ። መርካቶ ፡ የሚነግዱት ፡ ነጋዴ ዎች ፡[1] እነዚህን ፡ ተግባሮች ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደሚከተሉ ፡ ለመረዳት ፡ በመርካቶ ፡ ስለሚካሄዱ ፡ የንግድ ፡ ሥራዎች ፡ በአደረግነው ፡ ጥናት ፡ አንዳንድ ፡ ጥያቄዎች ፡ ቀጠ ይቀው ፡ ነበር ።

## ሀ. የንግድ ፡ ምዝገባ ፡ አስፈላጊነት ።

የንግድ ፡ ሥራ ፡ መዝገብ ፤ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ የንግድ ፡ መደ ብሮች ፡ እንዲመዘገቡ ፡ የንግድ ፡ ሥራዎች ፡ ምዝገባ ፡ ድንጋጌ ፡[2] ያስገድዳቸው ፡ ነበር ። የንግድ ፡ ሕጉ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡[3] መመዝገብን ፡ የሚመለከቱ ፡ ድንጋጌዎችን ፡ አጠቃ ልሎ ፡ ይይዛል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ተደንግጎ ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ አማካይነት ፡ ታትሞ ፡ በሚወጣ ፡ ትዕዛዝ ፡ መሠረት ፡ ካልተሻረ ፡ በስተቀር ፡ የቀድሞው ፡ ሕግ ፡ የጸና ፡ ሆኖ ፡ እንዲቆይ ፡ ይፈቅዳል ።[4] እስካሁን ፡ ድረስ ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ላይ ፡ ታትሞ ፡ የወጣ ፡ ትዕዛዝ ፡ የለም ። ነገር ፡ ግን ፡ ድንጋጌው ፡ በ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ. ምረቱ ፡ የንግድ ፡ ሥራዎች ፡ ምዝገባ ፡ አዋጅ ፡[5] ተተክቷል ። በንግድ ፡ ሕጉ ፡ መሠ ረት ፡ "ነጋዴዎች" ፡ በተባለው ፡ ቃል ፡ የሚጠሩትና ፡ "የንግድ ፡ ሥራን ፡ የሚሠሩ" ፡ ድርጅቶች ፡ ብቻ ፡ እንዲመዘገቡ ፡ ይገደዳሉ ። በአዋጁ ፡ መሠረት ፡ ግን ፡ ትርፍ ፡ በሚ ያስገኝ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የተሰማራ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ኩባንያ ፡ እን ዲመዘገብ ፡ ይገደዳል ። በንግድ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ያልተመዘገበ ፡ ሰው ፡ በወንጀለኛ ፡

---

* ጄ. ዲ. ፤ ፲፱፻፷፭ ፤ ኖርዝዌስተርን ፡ ዩኒቨርሲቲና ፡ ኤል ፡ ኤል ቢ ፤ ፲፱፻፷፯ ፤ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፤ የኖርዝዌስተርን ፡ ዩኒቨርሲቲና ፡ የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የምርምር ፡ ሥራ ፡ ዕቅድ ፡ አባሎች ፤ ፲፱፻፷፭ ።

1. የዚህ ፡ ጥናት ፡ ውጤት ፡ አጠቃላይ ፡ መግለጫ ፡ "በአዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ የሚካሄዱ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ዎች ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ ያላቸው ፡ አቋም ፤ ስለ ፡ መርካቶ ፡ ነጋዴዎችና ፡ አዲስ ፡ የወጡትንም ፡ ሕጎች ፡ እንዴት ፡ እንደሚጠቀሙባቸው ፡ የሚያሳይ ፡ አጭር ፡ መግለጫ ፡" በተባለው ፡ የፀሐፊው ፡ መጽሔት ፡ ውስጥ ፡ ይገኛል ። ይኸውም ፡ በ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ.ም. ታትሞ ፡ በወጣው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ውስጥ ፡ 'አኬዥናል ፡ ፔፐር ፡ ቁጥር ፡ ፩' በመባል ፡ ታትሞ ፡ ወጥቷል ።

2. በቁጥር ፡ ፳፯/፲፱፻፶ ፡ ዓ. ም. የንግድና ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሥራዎችን ፡ ስለ ፡ ማስመዝገብ ፡ የወጣ ፡ ድንጋጌ ፤ ነጋሪት ጋዜጣ ፤ አሥራ ፡ ሰባተኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፬ ።

3. የንግድ ፡ ሕግ ፤ ቁ. ፹፯—፺፫ ።

4. ኢድ ፤ ቁ. ፩ሺ፪፻፷፱ ።

5. አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፹፬/፶፬ ፡ ዓ. ም. የንግድና ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሥራዎችን ፡ ለማስመዝገብ ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፤ ነጋሪት ጋዜጣ ፤ ሀያ ፡ አንደኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፫ ።

መቅጫ ፡ ሕግ ፡[6] መሠረት ፡ ከሚደርስበት ፡ የወንጀለኛ ፡ ቅጣት ፡ በስተቀር ፡ "ነጋዴ" ፡ በሚል ፡ ስም ፡ ታውቆ ፡ ከሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ጋር ፡ እንዳይነግድ ፡ ሲከለከል ፡ በአዋጁ ፡ መሠረት ፡ ግን ፡ "ማናቸውም ፡ ኩባንያ ፡ ወይም ፡ ለብቻው ፡ የንግድ ፡ ወይም ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ማናቸውንም ፡ ኮንትራት ፡ ከማድረጉ ፡ በፊት ፤ በዚህ ፡ አዋጅ ፡ እንደተወሰነው ፡ አስቀድሞ ፡ በንግድና ፡ በኢንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ ካልተመዘገበ ፡ በቀር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በአደረገው ፡ በማናቸውም ፡ ኮንትራት ፡ ላይ ፡ ማናቸውንም ፡ ውሳኔ ፡ ለማድረግ ፡ መብት ፡ አይኖረውም ።"[7]

ባትጨማሪ ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤቶችም ፡ ላልተመዘገበ ፡ ንግድ ፡ የመነገጃ ፡ ፈቃድ ፡ እንዳይሰጡና ፡ ሳይመዘገብ ፡ በንግድ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የሚሰማራ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ ሳይመዘገብ ፡ ወይም ፡ በተመዘገበበት ፡ ንግድ ፡ በስተቀር ፡ በሌላ ፡ ዓይነት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ተካፋይ ፡ የሆነ ፡ በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ምሕረቱ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ይቀጣል ።[8] ምንም ፡ እንኳን ፡ የአዋጁ ፡ ድንጋጌዎች ፡ "ነጋዴዎችና ፡" "ነጋዴ ፡ ባልሆኑ ፡" ሰዎች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ረቂቅ ፡ የሆነ ፡ የሕግ ፡ ልዩነት ፡ አስቀርተው ፡ ማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ ንግድ ፡ እንዲመዘገብ ፡ ስለሚያዙ ፡ ቀለል ፡ ያሉ ፡ ቢሆኑም ፡ ምዝገባ ፡ አለማድረግ ፡ የሚያስከትሉት ፡ ቅጣቶች ፡ ከንግድ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይበልጥ ፡ አስቃቂ ፡ ናቸው ። በንግድ ፡ ሕጉ ፡ ሥር ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ንግዱን ፡ ያላስመዘገበ ፡ እንደሆነ ፡ ሊደርስበት ፡ የሚችለው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቅጣት ፡ የንግዱ ፡ የመለያ ፡ ምልክቶችና ፡ ስሙ ፡ ብቻ ፡ በሕግ ፡ አለመጠበቃቸው ፡ ነው ።[9] ኪሣራ ፡ ገብተሃል ፡ ተብሎ ፡ ከሚወሰንበት ፡ ይልቅ ፡ በገዛ ፡ ፈቃዱ ፡ የመጠበቂያ ፡ ስምምነት ፡ ሊያደርግ ፡ አይችልም ።[10] የሂሣብ ፡ መዝገቦቹም ፡ እሱን ፡ የሚጠቅሙ ፡ ማስረጃዎች ፡ ሆነው ፡ ሊቀርቡ ፡ አይችሉም ።[11]

እንደዚህ ፡ ያሉት ፡ ቅጣቶች ፡ በአነስተኛ ፡ ነጋዴዎች ፡ ላይ ፡ ሊደርሱ ፡ አይችሉም። ነገር ፡ ግን ፡ የአዋጁ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ልክ ፡ እንደተጻፉ ፡ በፍርድ ፡ ቤቶቹ ፡ ቢሠሩባቸው፡ ባንድ ፡ ባልተመዘገበ ፡ ነጋዴ ፡ የተፈረመ ፡ ውል ፡ እንዳይሠራበት ፡ ወይም ፡ እንዳይፈጸም ፡ ይከለክላሉ ።

<u>በመርካቶ ፡ ውስጥ ፡ ስለተመዘገቡ ፡ ንግዶች ፡ አመዘጋገብ ፡ የተደረገ ፡ የቃል ፡ መጠይቅ</u> ። የንግድ ፡ ሥራ ፡ የሚመዘገብበት ፡ ዋና ፡ ዓላማ ፡ የንግድ ፡ ይዞታው ፡ ምን ፡ እንደሆነና ፡ የተመዘገቡት ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ ድርጅቶች ፡ የገንዘብ ፡ ሁኔታ ፡ ለማሳወቅ ፡ ነው ።[12] ይህንን ፡ ዓላማ ፡ በማድረግ ፤ የተጠየቁት ፡ ሰዎች ፡ መመዝገብ ፡ ወይም ፡ አለመመዝገባቸውና ፡ ስለሌላ ፡ ዓይነት ፡ ንግዶች ፡ ለማወቅ ፡ በንግድ ፡ ሥራ ፡ መዝገብ ፡ መጠቀማቸውን ፡ ወይም ፡ አለመጠቀማቸውን ፡ ተጠየቁ ።

---

6. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፤ ቁ. ፻፷፰ ።
7. የንግድና ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሥራዎችን ፡ ለማስመዝገብ ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፤ ፲፱፻፶፬ ፤ ከላይ፡ በማስታወሻ ፡ ፩ ፡ ቁጥር ፡ ፫ ፡ ላይ ፡ ተጠቅሷል ።
8. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፤ ቁ. ፯፻፵፯ ።
9. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፻፲፫ ፤ ፻፳፮ —፻፵፮ ፡ ተመልከት (ቸ)።
10. ኢ.ድ ፤ ቁ. ፩ሺ፩፻፰ ።
11. ኢ.ድ ፤ ቁ. ፹፩ ።
12. <u>ኢ.ድ</u> ፤ ቁ. ፹፰ ፡ ኤ. ገዮርሬ ፡ <u>ማኑዌል ፡ ደ ፡ ድሩዋ ፡ ኮሜርሽያል</u> ፡ (ፓሪስ ፡ ሊብሬር ፡ ዠኔራል ፡ ደ ፡ ድሩዋ ፡ ኤ. ደ. ዠዩሪስፕሩደንስ ፤ ፲፱፻፶፯) ፤ ገጽ ፡ ፰ ።

የቃል ፡ መጠይቅ ፡ ከቀረበላቸው ፡ ሰዎች ፡ ውስጥ ፡ ከመቶ ፡ አርባ ፡ ሰባቱ ፡ በንግድና ፡ እንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ ዘንድ ፡ አልተመዘገብንም ፡ አሉ ። ካልተመዘገቡት ፡ ሰዎች ፡ ውስጥ ፡ ሁለቱ ፡ መረጃ ፡ ለማግኘት ፡ ያህል ፡ የሌሎቹን ፡ ንግዶች ፡ ፋይሎች ፡ (መዝገቦች) ፡ ተመልክተናል ፡ አሉ ። ከመቶ ፡ አርባ ፡ እጅ ፡ ደግሞ ፡ ተመዝግበናል ፡ አሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ከነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ውስጥ ፡ አራቱ ፡ ብቻ ፡ መረጃ ፡ ለማግኘት ፡ ሌሎቹን ፡ ፋይሎች ፡ (መዝገቦች) ፡ ተመልክተናል ፡ አሉ ። ከመቶ ፡ አሥራ ፡ ሦስቱ ፡ እጅ ፡ የሚሆኑት ፡ ደግሞ ፡ ምዝገባን ፡ ለሚመለከቱ ፡ ጥያቄዎች ፡ መልስ ፡ አልሰጡም ። ከቸርቻሪዎች ፡ ውስጥ ፡ የልብስና ፡ የጨርቃ ፡ ጨርቅ ፡ መደብሮች ፡ ከመቶ ፡ ውስጥ ፡ አርባ ፡ እጁ ፤ ከከባድ ፡ ዕቃዎችና ፡ ቁሳቁሶች ፡ ነጋዴዎች ፡ ውስጥ ፡ አሁንም ፡ ከመቶ ፡ አርባው ፡ እጅ ፤ በምግብ ፡ ሥራዎች ፡ ከተሠማሩት ፡ ውስጥ ፡ ከመቶ ፡ ሃያው ፡ እጅና ፡ ከአሥራ ፡ ሦስት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሸቀጦች ፡ ከሚነግዱት ፡ ሰዎች ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ ብቻ ፡ መመዝገባቸው ፡ ተረጋገጠ ። ከቡና ፡ ቤቶች ፤ ምግብ ፡ ቤቶችና ፡ ሆቴሎች ፡ መካከል ፡ ከመቶው ፡ ውስጥ ፡ ስድሣ ፡ አምስት ፡ እጅ ፡ ያህል ፡ ተመዝግበዋል ። ከእጅ ፡ ሥራ ፡ አዋቂዎችና ፡ የግል ፡ አገልግሎት ፡[13] ከሚሰጡት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ከመቶ ፡ አርባ ፡ እጁ ፡ ተመዝግበዋል ። ከአስመጪዎችና ፡ በጅምላ ፡ ከሚነግዱ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ከልብስና ፡ ጨርቃ ፡ ጨርቅ ፡ ነጋዴዎች ፡ ውስጥ ፡ ከመቶው ፡ ሰባ ፡ እጅ ፡ የሚሆኑት ፡ ሲመዘገቡ ፡ ከከባድ ፡ ዕቃዎችና ፡ የቤት ፡ መሥሪያ ፡ ዕቃዎች ፡ ነጋዴዎች ፡ ውስጥ ፡ ከመቶ ፡ ስድሣ ፡ አምስቱ ፡ ተመዝግበናል ፡ ብለዋል ።

በንግድ ፡ ማኅበር ፡ ዓይነት ፡ የሄድን ፡ እንደሆነ ፡ የግል ፡ ንግድ ፡ ካቋቋሙት ፡ ውስጥ ፡ ሰላሣ ፡ ሰባት ፡ ከመቶና ፡ የጽሑፍ ፡ ስምምነት ፡ ከሌላቸው ፡ በሽርክ ፡ ከሚነግዱት ፡ ሰዎች ፡ ውስጥ ፡ ሃያ ፡ ሁለት ፡ ከመቶ ፡ መመዝገባቸው ፡ ተረጋግጦአል ።[14] የጽሑፍ ፡ ስምምነት ፡ እያላቸው ፡ በሽርክና ፡ ከሚነግዱት ፡ ሰዎች ፡ ውስጥ ፡ ከመቶ ፡ ሰልሣ ፡ ሦስት ፡ እጅ ፡ ተመዝግበዋል ። በተጨማሪም ፡ ስምንት ፡ ከሚሆኑ ፡ ኃላፊነታቸው ፡ ከተወሰነ ፡ የግል ፡ ካምፓኒዎች ፡ ውስጥ ፡ አምስቱ ፤ አንድ ፡ የሆነው ፡ የተወሰነ ፡ ኃላፊነት ፡ ያለበት ፡ ማኅበርና ፡ አንድ ፡ የሆነው ፡ የአክሲዮን ፡ ካምፓኒ ፡ ተመዝግበዋል ። የንግድ ፡ ሥራ ፡ መዝገቡን ፡ ስለሌሎች ፡ ንግዶች ፡ ለማጥናት ፡ እንጠቀማለን ፡ ካሉት ፡ ስድስት ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ ውስጥ ፡ ሁለቱ ፡ ኃላፊነታቸው ፡ የተወሰነ ፡ የግል ፡ ካምፓኒዎች ፡ ናቸው ። ሌሎች ፡ አራቱ ፡ ደግሞ ፡ የግል ፡ ድርጅቶች ፡ ነበሩ ።

በንግድ ፡ ሥራ ፡ መዝገብ ፡ እንዳይጠቀሙ ፡ ፍላጎት ፡ የሚያሳጧቸው ፡ ብዙ ፡ ምክንያቶች ፡ አሉ ። ምንም ፡ እንኳን ፡ አዋጁ ፡ ንግዱ ፡ ያልተመዘገበ ፡ ነጋዴ ፡ ስለአንድ ፡ ውል ፡ ጉዳይ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ባሉት ፡ ፍ/ቤቶች ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ አይችልም ፡ ቢልና ፡ ንግዱ ፡ ካልተመዘገበ ፡ በስተቀር ፡ ማንኛውም ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ የንግድ ፡ ፈቃድ ፡ ለመስጠት ፡ አይችልም ፡ ቢልም ፡ እነዚህ ፡ መቀጫዎች ፡ በጠቅላላው ፡ በተግባር ፡ የተረሱ ፡ ይመስላል ። በመርካቶ ፡ የሚገኙት ፡ ታላላቅ ፡ ቋሚ ፡ ንግዶች ፡ በሙሉ ፡ በማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ የንግድ ፡ ፈቃድ ፡ የተሰጣቸው ፡ ናቸው ።

13. እነዚህ ፡ "ነጋዴዎች ፡" ወይም ፡ "የንግድ ፡ ሥራ ፡ ማኅበሮች ፡" ስላልሆኑ ፤ በንግድ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ መመዝገብ ፡ አይኖርባቸውም ። ነገር ፡ ግን ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ፳ ውስጥ ፡ በተጠቀሰውና ፡ በ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ. ም. በወጣው ፡ የንግድና ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሥራዎችን ፡ ለማስመዝገብ ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፡ በሚለው ፡ መሠረት ፡ መመዝገብ ፡ ይኖርባቸዋል ።

14. ያልተመዘገቡና ፡ ስምምነታቸውን ፡ በጽሑፍ ፡ ያላሰፈሩ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሮች ፡ ሕጋዊ ፡ አቋማቸው ፡ እንዴት ፡ እንደሆነ ፡ ለመረዳት ፡ ፓል ፡ ማኬርቲ ፡ "በሕግ ፡ ሳይታወቁ ፡ የሚሠሩ ፡" ("ደ ፡ ፋክቶ") እና ፡ ልማዳዊ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሮች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡" በሚል ፡ አርእስት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፤ ቮልዩም ፡ ፩ ፡ (፲፱፻፶፮ ፡ ዓ. ም.) ፤ ገጽ ፡ ፺፩ ፡ ላይ ፡ የጻፈውን ፡ ጽሑፍ ፡ ተመልከት (ች) ።

እንዲያውም ፡ አብዛኞቹ ፡ ታላላቅ ፡ የሆኑት ፡ ሕንፃዎች ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ ናቸው ። በጥናቱ ፡ ውስጥ ፡ ከተመረመሩት ፡ ጉዳዮች ፡ ውስጥ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ መዝገቡ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ተጠቅሶአል ። የተጠቀሰበትም ፡ ምክንያት ፡ ስሙ ፡ መዝገቡ ፡ ውስጥ ፡ ያልተመዘገበ ፡ ሰው ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ የአክሲዮን ፡ ኩባኒያ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ተብሎ ፡ ይጠራ ፡ ወይም ፡ አይጠራ ፡ እንደሆነ ፡ ለማወቅ ፡ በተደረገው ፡ ጥያቄ ፡ ነው ። የምዝገባው ፡ ሕግ ፡ ቢሠራበት ፡ ኖሮ ፡ ከሳሾቹ ፡ ስላልተመዘገቡ ፡ ከተመረመሩት ፡ ጉዳዮች ፡ ውስጥ ፡ አብዛኞቹ ፡ ውድቅ ፡ ይሆኑ ፡ ነበር ። ከተመዘገቡት ፡ ሰዎች ፡ ውስጥ ፡ አብዛኞቹ ፡ ሲናገሩ ፡ በመመዝገባቸው ፡ ምንም ፡ ያገኙት ፡ ጥቅም ፡ የለም ፡ ይላሉ ። አንዳንዶቹ ፡ ግን ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ንግድ ፡ ውስጥ ፡ ለመሳተፍና ፡ ከባንኮችም ፡ ብድርና ፡ ዋስትና ፡ ለማግኘት ፡ ይረዳል ፡ ብለዋል ። ጥቂቶች ፡ የባንክ ፡ ሠራተኞች ፡ ተጠይቀው ፡ ሲመልሱ ፡ ገንዘብ ፡ ሲያበድሩ ፡ ተበዳሪው ፡ ሰውዬ ፡ ንግዱን ፡ ማስመዝገቡን ፡ ወይም ፡ አለማስመዝገቡን ፡ እንመለከታለን ፡ አሉ ። አብዛኞቹ ፡ የባንክ ፡ ሠራተኞች ፡ ግን ፡ ጽኑ ፡ የሆነ ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ፈቃድ ፡ ከአለው ፡ ሕጋዊ ፡ የሆነ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ለመኖሩ ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ አድርገው ፡ ይቀበሉታል ። የንግድ ፡ መዝገብ ፡ መኖሩንና ፡ መመዝገብ ፡ እንዳለባቸው ፡ እያወቁ ፡ ካልተመዘገቡት ፡ ነጋዴዎች ፡ መሃከል ፡ ያላቸውን ፡ የንግድ ፡ ካፒታል ፡ (ዋና ፡ ገንዘብ) ፡ መናገር ፡ ስላለባቸውና ፡ ለምዝገባውም ፡ ገንዘብ ፡ መክፈል ፡ ስላለባቸው ፡ መመዝገቡ ፡ የበለጠ ፡ ግብር ፡ እንድንከፍል ፡ ያደርገናል ፡ የሚል ፡ ዐይነት ፡ አስተሳሰብ ፡ ነበር ። ስለግብር ፡ መክፈል ፡ የተደረገው ፡ ፍርሃት ፡ ያለምክንያት ፡ አይደለም ። በሚከተለው ፡ ክፍል ፡ እንደሚገለጸው ፡ ሁሉ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ግብር ፡ በገቢ ፡ ወይም ፡ በትርፍ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ቢመስ ምል ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የሚመሠረተው ፡ አንድ ፡ ንግድ ፡ ባለው ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ (ካፒታል) ፡ ላይ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ በመሠረቱ ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ የመመዝገቢያ ፡ መንገዶች ፡ አሉ ። አንዱ ፡ በንግድ ፡ ኢንዱስትሪና ፡ ቱሪዝም ፡ ሚኒስትር ፡ ዘንድ ፡ ሲሆን ፡ አንዱ ፡ ደግሞ ፡ በማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። አንድ ፡ ሰው ፡ ንግዱን ፡ ያላስመዘገበ ፡ እንደሆነ ፡ በማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ ስለሚቀጣና ፡ በንግድ ፡ ኢንዱስትሪና ፡ ቱሪዝም ፡ ሚኒስቴር ፡ ዘንድ ፡ የተመዘገበ ፡ እንደሆን ፡ ግብር ፡ ያስጨምራል ፡ ብሎ ፡ ስለሚፈራ ፡ አብዛኞቹ ፡ ነጋዴዎች ፡ ለንግድ ፡ ሥራ ፡ መክፈት ፡ ከማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ የንግድ ፡ ፈቃድ ፡ ማውጣቱ ፡ ብቻ ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ ይመስላቸዋል ።

## ሉ. <u>የሂሣብ ፡ መያዝ ፡ ግዴታዎችና ፡ ግብር ፡ ለመወሰን ፡ የሚሰጡት ፡ ጥቅም ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ አስፈላጊ ፡ ነጥቦች ።</u>

ነጋዴዎችና ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ድርጅቶች ፡ በሙሉ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ሂሣብ ፡ እንደሚይዙ ፡ የሚያመለክቱ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡[15] ውስጥ ፡ ይገኛሉ ። በጠቅላላ ፡ አስተያየት ፡ ማንም ፡ ሰው ፡[16] ወይም ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ በንግድ ፡ ሥራና ፡ ደንቦች ፡ የታወቁትን ፡ የሂሣብ ፡ ደብተሮች ፡ መያዝ ፡ አለበት ። ይህም ፡ የሚደረገው ፡ የሚካሄደው ፡ ንግድ ፡ ዓይነትና ፡ ጠቃሚነትን ፡ እየተመለከቱ ፡ ነው ።[17] አነስተኛ ፡

15. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፷፫—፷፮ ።
16. በፈረንሳይኛ ፡ የተጻፈው ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— “ቱት ፡ ፐርሶኔ ፡ ፊዚክ ፡ አያን ፡ ላ ፡ ኳሊቴ ፡ ደ ፡ ኮሜርሻንት ።”
17. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፷፪ ።

ነጋዴዎች ፡ (ቸርቻሪዎች) ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ሂሣብ ፡ እንዳይዙ ፡ በልዩ ፡ ደንቦች ፡[18] ይፈቅድላቸዋል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ ደንቦች ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ አልወጡም ። ቸርቻሪዎች ፡ የተባለውም ፡ ቃል ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ውስጥም ፡ ሆነ ፡ በሌላ ፡ ቦታ ፡ አልተተረጐመም ። ስለዚህ ፡ ምናልባት ፡ አነስተኛ ፡ ቸርቻሪውም ፡ ቢሆን ፡ አሁን ፡ በመመርመር ፡ ላይ ፡ ያለነውን ፡ አስፈላጊ ፡ ጉዳዮች ፡ መከተል ፡ ይኖርበት ፡ ይሆናል ።

በንግድ ፡ ሕጉ ፡ መሠረት ፡ ማንኛውም ፡ ነጋዴና ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ንግድ ፡ ቢሆን ፡ በየቀኑ ፡ የሚደረገውን ፡ ገቢና ፡ ወጭ ፡ የሚገልጽ ፡ አንድ ፡ የሂሣብ ፡ ደብተር ፡ መያዝ ፡ አለበት ። ሂሣብ ፡ ያዥ ፡ ከወር ፡ ውስጥ ፡ ቢያንስ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይህንን ፡ ሂሣብ ፡ ሊያስተካክል ፡ ይችላል ። ግን ፡ እነዚህን ፡ በየቀኑ ፡ የሚደረጉትን ፡ ሂሣብ ፡ ለማመሳከር ፡ እንዲያመች ፡ የሂሣብ ፡ ደብተሮቹንና ፡ መዝገቦቹን ፡ ማስቀመጥ ፡ አለበት ።[19] ማንኛውም ፡ ነጋዴና ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ በተጨማሪ ፡ የማመሳከሪያ ፡ ዝርዝርና ፡ ገቢና ፡ ወጭ ፡ የሚያሣይ ፡ ሂሣብ ፡ መያዝ ፡ አለበት ። ይህንንም ፡ ማዘጋጀት ፡ ያለባቸው ፡ ንግዱን ፡ ማካሄድ ፡ ሲጀምሩና ፡ የትርፍና ፡ የኪሣራ ፡ ሂሣብ ፡[20] ማጠናቀቅ ፡ በአለባቸው ፡ በየሂሣብ ፡ ዓመት ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ነው ። የሂሣብ ፡ አያያዙን ፡ በየጊዜው ፡ የማይከታተልና ፡ በጥሩ ፡ መልክ ፡ የማያስቀምጥ ፤ ደብዳቤዎቹን ፡ ካርኔዎቹን ፡ ሌሎቹንም ፡ የንግድ ፡ መዝገቦች ፡ በሕግ ፤ በደንብና ፡ በማኅበሩ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በተፈለጉት ፡ መሠረት ፡ የማይዝ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ በገንዘብ ፡ መቀጫ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ወር ፡ በማይበልጥ ፡ እሥራት ፡ ይቀጣል ።[21]

<u>የገቢ ፡ ግብር ፡ አዋጅና ፡ ደንቦች ፡ የሂሣብ ፡ አያያዝ ፡ አስፈላጊ ፡ ነጥቦች</u> ። በንግድ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ካሉት ፡ ግዴታዎች ፡ በተጨማሪ ፡ በንግድ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፡ በሙሉ ፡ በገቢ ፡ ግብር ፡ አዋጅና ፡[22] ደንቦች ፡[23] መሠረት ፡ ሂሣብ ፡ እንዲይዙ ፡ ግዴታ ፡ አለባቸው ። እነዚህ ፡ ሕጎች ፡ ቸርቻሪዎች ፡ ሂሣብ ፡ እንዳይዙ ፡ ይፈቅዱላቸዋል ። የገንዘብ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ግብር ፡ ከፋዮች ፡ የተወሰነ ፡ ፎርም ፡[24] ያላቸውን ፡ የሂሣብ ፡ መዝገቦች ፡ እንዲይዙ ፡ የሚያደርጉ ፡ ደንቦች ፡ ሊያወጣ ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ አንዳንዶቹ ፡ የግብር ፡ ከፋዮች ፡ እንዳይዙ ፡ ለማድረግም ፡ ደንቦችን ፡ ሊያወጣ ፡ ይችላል ። ይሄውም ፡ በግብር ፡ ተቀባይ ፡ ባለሥልጣን ፡ ውሳኔ ፡ መሠረት ፡ የሚቀረጠው ፡ ገቢያቸው ፡ ከ፭ሺ[25] (የኢትዮጵያ ፡ ብር) ፡ በላይ ፡ ላልሆኑ ፡ የግብር ፡ ከፋዮች ፡ ነው ። የገቢ ፡ ግብር ፡ ደንቦች ፡ የግብር ፡ ተቀባዮች ፡ ባለሥልጣን ፡ ገቢያቸው፡

18. እይ ፡ ቁ. ፷፬ ፤ በተጨማሪም ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ አውጪ ፡ ጉባኤ ፡ በኦክቶበር ፡ ፰ ፡ ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ. ም. የተነጋገረበትን ፡ ተመልከት ፡ (ቸ) ፡ ፕሮሴቨርፀ ፡ ደ ፡ ሉ ፡ ኮሚሲዮን ፡ ዴኮ ፡ ሎዋ ፡ ኮሜርሺያል ፡ (፲፱፻፶፬ ፤ ያልታተመ ፤ አርካይቭስ ፤ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፤ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ) ፡ ገጽ ፡ ፶፰ ።
19. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፷፯ ።
20. እይ ፡ ቁ. ፷፯ ።
21. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፬፻፲፯ ።
22. አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፻፹፫/፶፫ ፡ ዓ. ም. ከማናቸውም ፡ ገቢ ፡ ግብር ፡ ስለማስከፈል ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ሀያኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፲፫ ።
23. የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፶፰/፶፩ ፡ ዓ. ም. ፤ ስለገቢ ፡ ግብር ፡ የወጣ ፡ ደንብ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ሀያ ፡ ሁለተኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፩ ።
24. ከማናቸውም ፡ ገቢ ፡ ግብር ፡ ስለማስከፈል ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፤ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ. ም. ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ፳፪ ፡ ቁጥር ፡ ፴፪ ፡ ላይ ፡ ተጠቅሶአል ።
25. እይ. ቁ. ፶፫ ።

ከኢት. ፲ሺ. በታች ፡ ሆኖ ፡ ለተገመተ ፡ ግብር ፡ ከፋዮች ፡ ክፍል ፡ ሒሣብ ፡ እንዳይዙ ፡ ይደነግጋል ።[26] በተገመተው ፡ ገቢ ፡ ላይ ፡ የተመሠረቱ ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ ክፍሎች ፡ አሉ ። እያንዳንዱ ፡ ክፍል ፡ የሚከፍለውም ፡ የግብር ፡ መጠን ፡ ተገልጾአል ።

ግብር ፡ ከፋዩ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ሒሣብ ፡ ባይዝ ፤ ለአንድ ፡ ማንኛውም ፡ ምክን ያት ፡ የገቢ ፡ ግብር ፡ ባለሥልጣን ፡ የሒሣብ ፡ መዝገቦችን ፡ ካልተቀበላቸው ፡ ወይም ፡ የግብር ፡ ከፋይ ፡ ወይም ፡ ከፋይዋ ፡ በተባለው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ገቢውን ፡ ወይም ፡ ገቢ ዋን ፡ ያላስታወቁ ፡ እንደሆነ ፡ የገቢ ፡ ግብር ፡ ባለሥልጣን ፡ ግብሩን ፡ በግምት ፡ ሊወስን ፡ ይችላል ።[27]

<u>የመርካቶ ፡ ነግዶች ፡ የሒሣብ ፡ አያያዝ ፡ እንዴት ፡ እንደሆነ ፡ የተደረገ ፡ የቃል ፡ መጠይቅ</u> ። በንግድ ፡ ሕግና ፡ በገቢ ፡ ግብር ፡ አዋጅ ፡ ውስጥ ፡ የተዘረዘሩት ፡ ሒሣብ ፡ አያ ያዝ ፡ እንዴት ፡ እንደሚካሄድ ፡ ለማወቅና ፡ በንግድ ፡ ሥራም ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ውጤት ፡ እንዳለው ፡ ለመረዳት ፡ የመልስ ፡ መጠይቅ ፡ የተደረገላቸው ፡ ሰዎች ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ የሒሣብ ፡ ደብተር ፡ (መዝገብ) ፡ እንደሚይዙና ፡ (የያዙ ፡ እንደሆነ) ፡ የሚከ ፍሉትን ፡ ግብር ፡ ለመወሰን ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ይጠቅማሉ ፡ የሚሉ ፡ ጥያቄዎችን ፡ ተጠይቀዋል ። የኋለኛው ፡ ጥያቄ ፡ ይበልጥ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነ ፡ ይመስላል ። ይህም ፡ የሆነበት ፡ ምክንያት ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ግብሩን ፡ ለመወሰን ፡ የሚከተለው ፡ ዘዴ ፡ ነጋዴ ዎቹን ፡ ከሚያጋጥሙዋቸው ፡ ፕሮብሌሞች ፡ ሁሉ ፡ ዓቢይ ፡ ሆኖ ፡ ስለአገኙት ፡ ነው ። ከመቶ ፡ ሃምሣ ፡ ስምንት ፡ ተጠያቂዎች ፡ ውስጥ ፡ ስምንት ፡ ብቻ ፡ ሲቀሩ ፡ የቀሩት ፡ ሁሉም ፡ ለእነዚህ ፡ ጥያቄዎች ፡ መልስ ፡ ሰጥተዋል ። አምሣ ፡ ስድስቱ ፡ ምንም ፡ ዓይ ነት ፡ የሒሣብ ፡ ደብተር ፡ እንደማይዙና ፡ የሚከፍሉት ፡ ግብር ፡ የሚወሰነው ፡ በግምት ፡ ነው ፡ ብለዋል ። አምስቱ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ የሒሣብ ፡ ደብተር ፡ አንይዝም ፤ የም ንከፍለውም ፡ ግብር ፡ የለም ፡ ብለዋል ። እንደዚህ ፡ የሆነበትን ፡ ምክንያት ፡ በግልጽ ፡ ሊናገሩ ፡ አልቻሉም ። የቀሩት ፡ ሃምሣ ፡ አንዱ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ የሒሣብ ፡ ደብተር ፡ እንይዛለን ፡ ቢሆንም ፡ ግብሩ ፡ የሚወሰነው ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ በግምት ፡ ነው ፡ ብለ ዋል ። ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የሚይዙት ፡ ደብተሮች ፡ የማስታወሻ ፡ ደብተሮች ፡ ወይም ፡ "የመለማመጃ ፡ ደብተሮች ፡" ናቸው ። በነዚህም ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ የዱቤ ፡ ግዥና ፡ ሺያጮች ፡ ሲሆኑ ፡ የዕቃዎችንም ፡ ዝርዝር ፡ ጭምር ፡ ይይዛሉ ። ቢሆንም ፡ ትክክለኛ ፡ ስላልሆኑና ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ ስለተያዙ ፡ ትክክለኛውን ፡ ትርፋቸውንና ፡ ኪሣራቸውን ፡ ለመተለም ፡ የሚያስችሉ ፡ አይደሉም ።

አንዳንዶች ፡ ግን ፡ በቂ ፡ የሆኑ ፡ የሒሣብ ፡ ደብተሮች ፡ ይዘው ፡ ይገኛሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ በብዙ ፡ ምክንያቶች ፡ ለግብር ፡ መወሰኛ ፡ አይጠቀሙበትም ። አንዱ ፡ ነጋዴ ፡ የሒሣብ ፡ አያያዝ ፡ ትምህርት ፡ ተምሮ ፡ ስለነበር ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ የሒሣብ ፡ ደብተሮች ፡ በሙሉ ፡ ይዞ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ታክሱን ፡ የሚገምቱት ፡ ሰዎች ፡ እነዚ ህን ፡ የሒሣብ ፡ ደብተሮች ፡ ከመመርመር ፡ ፈንታ ፡ ታክሱን ፡ የሚወስኑት ፡ ደረሰኞቹን፡ ብቻ ፡ በመመልከትና ፡ በዓመት ፡ ውስጥ ፡ የተደረጉትን ፡ ሽያጮች ፡ በመገመት ፡

26. ስለገቢ ፡ ግብር ፡ የወጣ ፡ ደንብ ። ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ. ም. ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ፳፫ ፡ ቁ. ፴ ፡ ላይ ፡ የተገለጸ ።
27. ከማናቸውም ፡ ገቢ ፡ ግብር ፡ ስለማስከፈል ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ። ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ. ም. ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ፳፪ ፡ ቁ. ፵ ፡ ላይ ፡ የተጠቀሰው ።

ነው ። አንዱ ፡ ሰውዬ ፡ ደግሞ ፡ ሂሣብ ፡ መያዝ ፡ ከጀመርኩ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ሆኖኛል ፤ ነገር ግን ፡ የገቢ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፤ አልተቀበላቸውም ፡ ብሏል ። ግብሩም ፡ እንዲቀነስለት ፡ ነገሩን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለፍ/ቤት ፡ አቅርቦ ፡ ነበር ። አንዱ ፡ ደግሞ ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ መጽሔትና ፡ የሂሣብ ፡ ሠንጠረዦች ፡ ከአማርኛና ፡ እንግሊዝኛ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ ጭምር ፡ እንዳለው ፡ ለጠያቂው ፡ ካስረዳ ፡ በኋላ ፡ እንደዚህም ፡ ሆኖ ፡ እነዚህ ፡ መጻሕፍትና ፡ የሂሣብ ፡ ደብተሮች ፡ በየጊዜው ፡ ስለማይፈተሹ ፡ ለግብር ፡ መወሰኛ ፡ አይጠቀሙም ፡ አለ ። አሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዎች ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ የሂሣብ ፡ ደብተሮችን ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ቢያንስ ፡ ፋክቱሮችንና ፡ ደረሰኞችን ፡ እንይዛለን ፤ ግብር ፡ ወሳኞቹም ፡ ይመለከቱታል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በራሳቸው ፡ ግምት ፡ ያከሉታል ፡ ብለዋል ።

ጥያቄዎቹን ፡ ከመለሱት ፡ ሰዎች ፡ መሃከል ፡ አንድ ፡ ስድስተኛው ፡ ብቻ ፡ ግብር ፡ ወሳኞቹ ፡ በግምት ፡ ሳይሆን ፡ ግብሩን ፡ በሂሣባችን ፡ መሠረት ፡ የሚወስኑበት ፡ የሂሣብ ፡ መጽሔቶችና ፡ ሠንጠረዦችን ፡ እንይዛለን ፡ አሉ ። ሦስት ፡ ደግሞ ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ የሂሣብ ፡ ደብተሮች ፡ የሚይዙ ፡ መሆናቸውን ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አሁን ፡ በቅርቡ ፡ ንግድ ፡ የጀመሩ ፡ ስለሆነ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ የሚከፍሉት ፡ ግብር ፡ ያልተወሰነ ፡ መሆኑን ፡ ገልጸዋል ።

ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ዕቃዎችን ፡ የሚሸጡት ፡ ነጋዴዎች ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ የሂሣብ ፡ መዝገቦች ፡ አይዙም ፤ የተያዙ ፡ የሂሣብ ፡ ደብተሮች ፡ ቢኖሩም ፡ ለግብር ፡ መወሰኛ ፡ አያገለግሉም ። ይህም ፡ አስተያየት ፡ ከመቶ ፡ ዘጠና ፡ እጅ ፡ የሚሆኑትን ፡ ከባድ ፡ ዕቃዎችና ፡ የቤት ፡ ዕቃዎች ፡ ቸርቻሪዎችን ፤ ከመቶ ፡ ሰማኒያ ፡ አምስት ፡ እጅ ፡ የሚሆኑትን ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ አዋቂዎችና ፡[28] የግል ፡ ንግድ ፡ አቋቁመው ፡ አገልግሎት ፡ የሚሰጡት ፡ ሰዎችን ፤ በምግብ ፡ ሸቀጥ ፡ ውስጥ ፡ ተካፋይ ፡ ከሆኑት ፡ ከመቶ ፡ ሰማኒያው ፤ ከመቶ ፡ ሰባ ፡ አምስት ፡ የሚሆኑ ፡ ቡና ፡ ቤቶች ፤ ሆቴሎችና ፡ ምግብ ፡ ቤቶች ፡ እና ፡ ከመቶ ፡ ስድሣ ፡ ሰባት ፡ እጅ ፡ የሚሆኑትን ፡ የልብስና ፡ ጨርቃ ፡ ጨርቅ ፡ ቸርቻሪዎችን ፡ ይመለከታል ። ለግብር ፡ መወሰኛ ፡ የሚረዱት ፡ ወይም ፡ ከግምት ፡ ጋር ፡ ታክለው ፡ የሚሠራባቸው ፡ ሂሣቦች ፡ ግን ፡ ከመቶ ፡ ሰባ ፡ አምስት ፡ እጅ ፡ በሚሆኑ ፡ በከባድ ፡ ዕቃና ፡ የቁሳቁስ ፡ ዕቃዎችን ፡ አስመጪዎችና ፡ የጅምላ ፡ ነጋዴዎች ፡ ከመቶ ፡ ሰባ ፡ እጅ ፡ በሚሆኑት ፡ የልብስና ፡ የጨርቃ ፡ ጨርቅ ፡ አስመጪዎችና ፡ በጅምላ ፡ ሻጮች ፡ ይያዛሉ ።

የንግድ ፡ ድርጅቶችን ፡ አቋም ፡ ስንመለከት ፡ ግላዊ ፡ ተራ ፡ ንግድ ፡ ከሚነግዱት ፡ ውስጥ ፡ ከመቶ ፡ ሰባ ፡ አምስትና ፡ የጽሑፍ ፡ ስምምነት ፡ ከሌላቸው ፡ በሽርክና ፡ ከሚነግዱት ፡ ከመቶ ፡ ሰማኒያ ፡ እጅ ፡ ለግብር ፡ መገመቻ ፡ የሚሆን ፡ ሂሣብ ፡ አልያዙም ። ከመቶ ፡ ስድሣ ፡ አምስት ፡ እጅ ፡ የሚሆኑት ፡ ኃላፊነታቸው ፡ የተወሰነ ፡ የግል ፡ ኩባኒያዎች ፡ እና ፡ ከመቶ ፡ ሰባ ፡ እጅ ፡ የሚሆኑት ፡ የጽሑፍ ፡ ስምምነት ፡ ያላቸው ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሮች ፡ ሂሣብ ፡ መያዛቸው ፡ ተረጋግጦአል ። ስለዚህ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ሂሣብ ፡ ወይም ፡ ደንበኛ ፡ የሆነ ፡ የሂሣብ ፡ አያያዝ ፡ ዘዴ ፡ የሌላቸው ፡ በእያንዳንዱ ፡ ባለቤት ፡ የሚካሄዱት ፡ ትናንሽ ፡ የችርቻሮ ፡ ሱቆች ፡ ወይም ፡ ያልታወቁ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሮች ፡ ቢሆኑም ፡ ትላልቅ ፡ የሆኑ ፡ አያሌ ፡ አስመጪዎችና ፡ በጅምላ ፡ የሚነግዱት ፡ ድርጅቶች ፡ ደንበኛ ፡ የሂሣብ ፡ መዝገብ ፡ ያላቸው ፡ አይመስልም ።

---

28. ከነዚህ ፡ ውስጥ ፡ አብዛኛዎቹ ፡ "የነጋዴነት ፡ አቋም ፡ ስለሌላቸው ፡" በንግድ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የሂሣብ ፡ መዝገብ ፡ እንዲኖራቸው ፡ አይገደዱም ።

ደንበኛ ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ሂሣብ ፡ እያያዝ ፡ እንዲከተሉ ፡ ማድረግ ፡ ቀላልና ፡ በፍጥነት ፡ የሚፈጸም ፡ ሥራ ፡ አይደለም ። ይህን ፡ ለማድረግ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ከተደረገ ፡ መኃይም ፡ ሆነው ፡ የሂሣብ ፡ አያያዝ ፡ ዘዴ ፡ የማያውቁትንና ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ቀጥረው ፡ እንዲያሠሩ ፡ ንግዳቸው ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ያልደረጀውን ፡ ወይም ፡ ያልተስፋፋውን ፡ ሰዎች ፡ ከንግድ ፡ ሥራ ፡ ውጪ ፡ ሊያደርጋቸው ፡ ይችላል ። ቢሆንም ፡ ነጋዴዎች ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ሂሣብ ፡ እንዲይዙ ፡ የግብር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የሚገፋፉ ፡ ይመስላል ። ይህም ፡ መረጃ ፡ የተገኘው ፡ አንዱ ፡ ሰው ፡ ሲጠየቅ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ የሂሣብ ፡ መዝገብ ፡ አልይዝም ፡ ነበር ፤ ካሁን ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ እይዛለሁ ፡ ምክንያቱም ፡ ባለፈው ፡ ዓመት ፡ መዝገብ ፡ ባለመያዜ ፡ ብቻ ፡ ሃያ ፡ ብር ፡ ተቀጣሁ ፡ ብሏል ። ግን ፡ አንድ ፡ ነጋዴ ፡ ሲናገር ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ የሂሣብ ፡ ደብተሮች ፡ ካላሰናዳሁ ፡ በዓመት ፡ ውስጥ ፡ የኢት. ብር ፡ ፻፶ መቀጫ ፡ መክፈል ፡ ቢኖርብኝም ፡ ሂሣቡን ፡ የሚያጠናቅቅ ፡ ሰው ፡ ቀጥሬ ፡ ለማሠራት ፡ በወር ፡ ከኢት. ብር ፡ ፻፶ በላይ ፡ መክፈል ፡ አለብኝ ። ሁለተኛውን ፡ ለማድረግ ፡ ስለማልችል ፡ አንደኛውን ፡ መርጫለሁ ፡ አለ ። ደንበኛ ፡ የሂሣብ ፡ አያያዝ ፡ ሲስቴም ፡ ያለመኖር ፡ የአብዛኞቹን ፡ ንግዶች ፡ ይዞታ ፡ የሚያናጋ ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ ትርፍ ፡ ያላቸውን ፡ የዕቃዎች ፡ ዋጋ ፡ ለመወሰንና ፡ አዲስ ፡ ንግዶችን ፡ ለማቋቋም ፡ ውሳኔ ፡ ለማድረግ ፡ ሂሣብ ፡ መያዝ ፡ አስፈላጊ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ግብር ፡ የመወሰኛው ፡ ዘዴ ፡ እኩልና ፡ ትክክል ፡ ስላልሆነ ፡ ለንግድ ፡ ዕድገት ፡ እንቅፋት ፡ ነው ። ግብር ፡ ከፋዮች ፡ የግብር ፡ ወሳኞችን ፡ ግምት ፡ መቃወሚያ ፡ የመዝገብ ፡ ማስረጃ ፡ ስለማይኖራቸው ፡ ግብር ፡ ወሳኞቹ ፡ ንግዱ ፡ የሚያደርገውን ፡ ትርፍ ፡ በራሳቸው ፡ አስተያየት ፡ ገምተው ፡ መወሰን ፡ ጉቦ ፡ እንዲቀበሉ ፡ ሊገፋፋቸው ፡ ይችላል ። ስለ ፡ ግብር ፡ ችግራቸው ፡ ትችት ፡ ያቀረቡት ፡ ነጋዴዎች ፡ በሙሉ ፡ ሲመልሱ ፡ ብዙዎቹ ፡ የመርካቶ ፡ ሰዎች ፡ አግባብ ፡ ያልሆነ ፡ ግብር ፡ ከመክፈል ፡ ለግብር ፡ ተቀባዮች ፡ ጉቦ ፡ ይሰጣሉ ፡ አሉ ፤ እንዲያውም ፡ ብዙዎቹ ፡ እራሳቸው ፡ በእጃቸው ፡ ጉቦ ፡ መስጠታቸውን ፡ አረጋገጡ ። ስለዚህ ፡ ነጋዴዎች ፡ ደንበኛ ፡ የሂሣብ ፡ መዝገብ ፡ እንዲይዙ ፡ ለማድረግ ፡ ሙከራ ፡ መደረግ ፡ አለበት ። ነገር ፡ ግን ፡ ሕጎቹን ፡ በፍጥነት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ማዋል ፡ ያልተፈለጉትን ፡ ውጤቶች ፡ ወይም ፡ ጠንቆች ፡ ሊያስከትል ፡ ይችላል ።

## ሐ. <u>ኪሣራ ።</u>

<u>የሕጉ ፡ መጽሐፍ ፡ ድንጋጌዎች</u> ። በሕጎቹ ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ ነጋዴ ፡ ያልሆነ ፡ ሰው ፡ ግዴታዎቹን ፡ ለመፈጸም ፡ የገንዘብ ፡ አቅም ፡ ካነሰው ፤ አበዳሪዎቹ ፡ (ባለገንዘቦቹ) ፡ የፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ውሣኔ ፡ በመከተል ፡ ለራሱና ፡ ለቤተሰቡ ፡ መተዳደሪያ ፡ ከሆኑት ፡ ነገሮች ፡ በስተቀር ፡ የባለዕዳውን ፡ ንብረት ፡ ሊይዙ ፡ ይችላሉ ።[29] ቀደም ፡ ብለው ፡ ያመለከቱት ፡ ሰዎች ፡ የተገኘውን ፡ ሊወስዱ ፡ ይችላሉ ፤ ቢሆንም ፤ ባዶ ፡ እጃቸውን ፡ የቀሩት ፡ ሰዎች ፡ መብት ፡ ግን ፡ አይነካም ፤ ምንም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ ባለመብትነታቸውን ፡ ሊቀዳጁ ፡ ይችላሉ ። በሌላ ፡ አነጋገር ፡ "ነጋዴ ፡ ያልሆነ" ፡ ባለዕዳ ፡ በሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ዕዳዎቹን ፡ እንዳይከፍል ፡ ይቅርታ ፡ ሊደረግለት ፡ አይችልም ። "ከሥሯል" ፡[30] ተብሎ ፡ ማረጋ

---

29. የፍት.ሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፩፻፰—፩፻፲፩ ።
30. <u>ኢ.ድ.</u> ቁ. ፫፻፺፯(፪) ፤ የመክሰር ፡ ድንጋጌዎችን ፡ ነጋዴ ፡ ባልሆኑ ፡ ሰዎችም ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ለማድረግ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ አውጪው ፡ ጉባኤ ፡ ተነጋግሮበት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ሕጉን ፡ ባረቀቀው ፡ ሰው ፡ ብርታት ፡ ሐሳቡ ፡ ውድቅ ፡ ሆኗል ።
<u>ፕሮሴ ፡ ብርቦ</u> ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ፲፰ ፤ ገጽ ፡ ፭፻፰ ፡ ላይ ፡ ተገልጾአል ።

ገሚ ፡ ሊሰጠው ፡ አይችልም ። ባለዕዳው ፡ ገንዘብ ፡ ለመክፈል ፡ ካልቻለ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ትዕዛዝ ፡ ለመፈጸም ፡ አልፈለገም ፡ ተብሎ ፡ ሊታሠር ፡ አይችልም ።[31] በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ ነጋዴ ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ እነርሱ ፡ ወይም ፡ ባለገን ዘቦቹ ፡ ጉዳዩን ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ካቀረቡ ፡ ከሥኖል ፡ ተብሎ ፡ ሊረጋገጥ ፡ ይችላል ።

ስለኪሣራ ፡ ጉዳይ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ድርጅት ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ያነሳ ፡ እንደሆነ ፡ ዕዳውን ፡ ለመክፈል ፡ ያልቻለ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ ይህንኑና ፡ የንግዱን ፡ የሒሣብ ፡ ይዞታ ፤ የትርፉንና ፡ ኪሣራ ፡ ሒሣብ ፤ የንግድ ፡ ብድሩ ንና ፡ ዕዳ ፡ የሚገልጽ ፡ ማስታወቂያ ፡ ስለኪሣራ ፡ ጉዳይ ፡ ለሚሰማው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።[32] በዚህ ፡ መሠረት ፡ ባለዕዳ ፡ ዕዳውን ፡ በከፊል ፡ እንኳን ፡ ከፍሎ ፡ ንግዱን ፡ የሚቀጥልበት ፡ ወይም ፡ ንግዱ ፡ እንዲቆም ፡ ተደርጎ ፡ ቀሪ ፡ የሆነው ፡ ሀብት ፡ በባለገንዘቦች ፡ መሃከል ፡ የሚከፋፈልበት ፡ የተወሳሰበ ፡ ሥርዓት ፡ ይጀምራል ። የባለ ዕዳው ፡ ሀብት ፡ ከኢት. ፩ ሺህ ፡ ብር ፡ በላይ ፡ ካልሆነ ፡ ወይም ፡ የዕዳው ፡ አንድ ፡ አሥ ረኛ ፡ ካልሆነ ፡ በተራ ፡ ጊዜ ፡ የሚደረገው ፡ ሥርዓት ፡ ቀርቶ ፡ አፋጣኝና ፡ አጠር ፡ ያለ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ይወሰዳል ።[33] ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ የኪሣራ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ከመ ደረጉ ፡ ይልቅ ፡ ዕዳውን ፡ ለመክፈል ፡ ይሳነኛል ፡ ብሎ ፡ የሚገምት ፡ ባለዕዳ ፡ ከባለገን ዘቦቹ ፡ ጋር ፡ የሚያስማማ ፡ አንድ ፡ የመጠበቂያ ፡ ስምምነት ፡ እንዲፈጠርለት ፡ በገዛ ፡ ፈቃዱ ፡ ሊጠይቅ ፡ ይችላል ።[34] ነገር ፡ ግን ፡ ይህንን ፡ ለማድረግ ፡ የፈለገ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ኪሣራን ፡ ለማስታወቅ ፡ የሚፈለጉትን ፡ መዝገቦች ፡ አቅርቦ ፡ ንግዱን ፡ ከጀመረ ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ ወዲህ ፡ በደንቡ ፡ መሠረት ፡ መመዝገቡን ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።[35]

<u>በመርካቶ ፡ ኪሣራ ፡ በልማድ ፡ እንዴት ፡ እንደሚፈጸም</u> ። በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ የተገኘው ፡ ጥናት ፡ በግልጽ ፡ እንደሚያስረዳው ፡ እነዚህ ፡ ስለ ኪሣራና ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆኑትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ መርካቶ ፡ ውስጥ ፡ ባሉት ፡ ንግዶች ፡ ላይ ፡ መጠቀም ፡ ያዳግታል ፤ ምክንያቱም ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የሚመዘገቡ ፡ ስለማይ ሆኑና ፡ የሒሣብ ፡ መዝገቦችን ፡ ስለማይዙ ፡ ነው ። በከፍተኛ ፡ ፍ/ቤት ፡ ቀርቦ ፡ ያገኘ ነው ፡ አንድ ፡ የኪሣራ ፡ ክስ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ እርሱም ፡ የአንድ ፡ የአክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ ሥራ ፡ ማቆምን ፡ የሚመለከት ፡ ነው ።

ኪሣራ ፡ በመርካቶ ፡ ነጋዴዎች ፡ በዘልማድ ፡ ታውቆ ፡ የሚሠራበት ፡ ነው ። ቢሆንም ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንደተጠቀሰው ፡ የሽምግልናና ፡ የእርቅ ፡ ውጤቶች ፡ ስለ ኪሣራ ፡ ከሚደረገው ፡ ዳኝነት ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆኑ ፡ ውጤቶች ፡ አሏቸው ። ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ይህንን ፡ ነገር ፡ የሚመለከት ፡ አንድ ፡ አስመጪ ፡ የሆነ ፡ ዓረብ ፡ ባንድ ፡ "በከሰረ" ፡ ነጋዴ ፡ ላይ ፡ የኢት. ፩ ሺህ ፡ ብር ፡ የተስፋ ፡ ሰነድ ፡ ይዞ ፡ ነበር ። የከሠረው ፡ ዓረብ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፩ሺህ ፡ ብር ፡ የሚያወጡ ፡ ዕቃዎች ፡ ከተለያዩ ፡ አሥር ፡ ከሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ተቀብሎ ፡ ነበር ። ያለው ፡ ግን ፡ የኢት. ፯ ሺህ ፡ ብር ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ የሚያውቋቸውና ፡ ሁሉም ፡ የተስማሙበት ፡ ስድስት ፡ ሽማ

31. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፤ ቁ. ፫፻፹፪ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቁ. ፺፰ ።

32. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፱፻፸፱ — ፱፻፹፫ ።

33. <u>ኢ.ድ.</u> ቁ. ፩ሺ፩፻፷፯ ።

34. <u>ኢ.ድ.</u> ቁ. ፩ሺ፩፻፲፱ — ፳፫ ።

35. <u>ኢ.ድ.</u> ቁ. ፩ሺ፩፻፹ ።

ግሌዎች ፡ ተመረጡ ። የእርቁ ፡ ስምምነት ፡ አልተጻፈም ፡ ነበር ፤ ስለዚህ ፡ የሥርዓቶቹ፡ ዓላማ ፡ ወገኖቹን ፡ ሁሉም ፡ በተስማሙበት ፡ ለማስታረቅ ፡ የተደረገ ፡ ሙከራ ፡ ነበር ። በየሳምንቱ ፡ አራት ፡ ጊዜ ፡ ያህል ፡ ይሰበሰቡ ፡ ነበር ። በመጀመሪያ ፡ ባለዕዳው ፡ የመጨረሻ ፡ ሀብቶቹን ፡ ለመስጠት ፡ ፍላጎት ፡ አልነበረውም ። በመጨረሻ ፡ ግን ፡ በሽማግሌዎች ፡ መገፋፋትና ፡ ብርታት ፡ ሊስማማ ፡ ቻለ ። ቀረጦቹን ፡ ከከፈለ ፡ በኋላ ፡ ሽማግሌዎቹና ፡ ባለገንዘቦች ፡ ሀብቱ ፡ እንዴት ፡ እድርጎ ፡ እንደሚከፋፈል ፡ ተነጋገሩ ። ባለገንዘቦቹ ፡ የተስፋ ፡ ሰነዶቹን ፡ ቀዳደው ፡ የዕዳውን ፡ ግማሽ ፡ እንዲቀበሉ ፡ በማለት ፡ ሽማግሌዎቹ ፡ ወሰኑ ። ውሳኔው ፡ በወረቀት ፡ ላይ ፡ አልሰፈረም ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የተስፋ፡ ሰነዶቹ ፡ በሽማግሌዎቹ ፡ ፊት ፡ ተቀዳደው ፡ ስለነበር ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ነገሩ ፡ እዲስ ፡ ሆኖ ፡ ሊነሳ ፡ የሚችል ፡ አይመስልም ። ውሳኔውን ፡ ሁሉም ፡ ሰው ፡ ተቀብሎታል ። ተጠያቂውም ፡ በመልሱ ፡ ላይ ፡ ውሳኔውን ፡ ባላከበረ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ምን ፡ እርምጃ ፡ ይወሰድ ፡ እንደነበር ፡ አላውቅም ፡ ብሏል ።

አንዱ ፡ ሽማግሌ ፡ ሲጠየቁ ፡ እንዲህ ፡ አሉ ። ነጋዴዎች ፡ ሲከስሩ ፡ ደብዳቤ ፡ አዞረው ፡ ለሚያውቁዋቸው ፡ ሰዎች ፡ ለምን ፡ እንደከሰሩ ፡ መግለጽና ፡ ያለባቸውን ፡ ዕዳ ፡ ለመክፈል ፡ እርጥባን ፡ መጠየቅ ፡ የተለመደ ፡ ነገር ፡ ነው ። ሽማግሌው ፡ ይህንን ፡ ጥያቄ፡ ሲመልሱ ፡ በቅርቡ ፡ መደብሩ ፡ ከተቃጠለ ፡ ሰው ፡ የተላከላቸው ፡ አንድ ፡ ደብዳቤ ፡ በኪሳቸው ፡ ውስጥ ፡ ይዘው ፡ ነበር ። አብዛኛው ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ እርጥባን ፡ እንዲያደርግ ፡ ኅብረተሰቡ ፡ የሚያስገድደው ፡ ይመስለዋል ። እላይ ፡ እንደተገለጸው ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ዕድር ፡ እንደ ፡ ኪሣራ ፡ ዋስትና ፡ ሆኖ ፡ ይቆጠራል ። አንዱ ፡ ዕድርተኛ ፡ በእውነት ፡ ከሥሮ ፡ እንደሆን ፡ ዕድሩ ፡ ዕዳውን ፡ ይከፍልለታል ።

በልምድ ፡ የሚሠራባቸው ፡ የኪሣራ ፡ ሥርዓቶች ፡ ባለዕዳዎቹንና ፡ ባለገንዘቦቹን ፡ እንዲደግፍ ፡ ተብሎ ፡ የወጣውን ፡ የኪሣራ ፡ ሕጎች ፡ በሙሉ ፡ አይዙም ። ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህን ፡ የኪሣራ ፡ ምርመራ ፡ ሥርዓት ፡ የሚያካሄዱት ፡ ሽማግሌዎች ፡ የመከፈያ ፡ ቀናቸው ፡ የደረሰውን ፡ ዕዳዎች ፡ ይመረምራሉ ፤ ባለዕዳውን ፡ ጥሩ ፡ አድርገው ፡ ስለሚያውቁ ፡ ስለሀብቱ ፡ አጠናቀው ፡ ያውቃሉ ፡ ማለት ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ የተደረጉት ፡ ስምምነቶች ፡ በሕግ ፡ "የግልግል"[36] ፡ ውጤት ፡ ስላላቸው ፡ ባለገንዘቦቹ ፡ በኋላ ፡ ፍ/ቤት ፡ ሄደው ፡ ክሳቸውን ፡ እንደገና ፡ ሊመሠርቱ ፡ አይችሉም ።

በጠቅላላው ፡ የኪሣራ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በጣም ፡ የተወሳሰቡና ፡ ከብዙ ፡ የንግድ ፡ ተግባሮች ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ የሌላቸው ፡ ስለሆኑ ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ካሉት ፡ የባዕድ ፡ ክፍሎች ፡ ውስጥ ፡ እነርሱ ፡ ይበልጡኑ ፡ "አይሠራባቸውም" ። ነገር ፡ ግን ፡ ኪሣራን ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦች ፡ እንዲኖሩ ፡ በማስፈለጉ ፡ በሕግ ፡ ታውቀው ፡ ሊሠራባቸው ፡ የሚቻሉ ፡ ብዙ ፡ የልምድ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቶች ፡ ሊፈጠሩ ፡ ችለዋል ።

36. በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ አስታራቂው ፡ ያደረጋቸውን ፡ የግልግል ፡ ቃሎች ፡ ለማረጋገጥ ፡ በጽሑፍ ፡ በግልጽ ፡ ግዴታ ፡ ካልገቡ ፡ ሊገደዱ ፡ አይችሉም ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፩ሺ፯፻፴፩(፪)። ተዋዋዮቹ ፡ ወገኖች ፡ ግልግሉ ፡ ይግባኝ፡ ሳይኖረው ፡ መጨረሻ ፡ ሆኖ ፡ እንደተፈረደ ፡ ፍርድ ፡ ሥልጣን ፡ አለው ፡ ብለው ፡ በስማሙና ፡ ግልግል ፡ ያደረጉበትን ፡ መብቶች ፡ በመመልከት ፡ በተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ ወይም ፡ ከነርሱ ፡ ባንዱ ፡ በተደረገው ፡ ስሕተት ፡ ምክንያት ፡ ግልግል ፡ ሊነካ ፡ አይችልም ፡ የሚለውን ፡ ቢቀበሉም ፡ ኢ.ድ. ቁ. ፩ሺ፯፻፲፪ ፤ ግልግል ፡ ፈራሽ ፡ ሊሆን ፡ የሚችልበት ፡ አንዳንድ ፡ ምክንያቶች ፡ አሉ ። ኢ.ድ. ቁ. ፩ሺ፯፻፲፫ — ፲፮ ።

## መደምደሚያ ።

በመርካቶ ፡ ውስጥ ፡ በሕግና ፡ በልምድ ፡ መሃከል ፡ ዐቢይ ፡ የሆኑ ፡ ልዩነቶች ፡ መኖራቸውን ፡ የዚህ ፡ ምርምር ፡ ውጤቶች ፡ ሊገልጹ ፡ ችለዋል ። እነዚህ ፡ ልዩነቶች ፡ ሊፈጠሩ ፡ የቻሉት ፡ ስሊሂሣብ ፡ አያያዝና ፡ ምዝገባ ፡ ነጋዴዎች ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ትምህርትና ፡ ዕውቀት ፡ ስለሌላቸውና ፡ ባለሥልጣኖቹም ፡ ከባድ ፡ የሆኑትን ፡ የሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ከማዋል ፡ ችላ ፡ በማለታቸው ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ሕጎች ፡ ለአገሪቷ ፡ "ባዕድ ፡" ስለሆኑና ፡ የንግድ ፡ ልምዶቹዋን ፡ ስለሚንጻረሩ ፡ አንቀበላቸውም ፡ የሚል ፡ ስሜት ፡ አላገኘንም ፡ ብናገኝም ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ ነው ።

ነጋዴዎቹ ፡ ሕጎችና ፡ ጥቅማቸው ፡ እየገባቸው ፡ ሲሄድ ፡ እነዚህን ፡ ሕጎች ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ሊጠቀሙባቸውና ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሊያውሏቸው ፡ የሚችሉ ፡ ይመስላል ።